የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 236212

ጥር 25 ቀን 2018 ዓ/ም

ዳኞች፡- ቴዎድሮስ ምህረት

ብርሃኑ አመነው

ገበየሁ ፈለቀ

ተሾመ ሽፈራው

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ

2. አቶ ፍቃዱ ዳባ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መሉጌታ ደጀኑ

2. ወ/ሮ እህተማሪያም በዛብህ

<u>ፍርድ</u>

ይህ ጉዳይ በአንድ መዝገብ ላይ በተሰጠ ውሳኔ መብቱ ተነክቷል የሚል ሦስተኛ ወገን በሌላ መዝገብ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡

1. የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት አቶ ኃይለ ወልዴ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 15 ዉስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 033 የሆነው የአውራሹ የወ/ሮ ስንቅነሽ ወልዴን ቤት በሽያጭ ለማስተላለፍ በአሁን ተጠሪዎች መካከል የተደረገ ውል እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቁን ተከትሎ ተጠሪዎች ለክሱ ከሰጡት መልስ በተጨማሪ የስር ከሳሽ በሽያጭ ውሉ መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እንዲያስረክባቸው ዳኝነት በመጠየቅ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ክርክሩን በመ/ቁጥር 00867 ላይ መርምሮ የስር ከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን 2ኛ አመልካች በሌላ መዝገብ ላይ በተደረገ ክርክር ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እንዲረከብ በፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ቤቱን መረከቡን ጠቅሶ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሰረት ያቀረበውን የመቃወም

አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ በማለት ሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሰርዞታል፡፡

2. ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 122926 ላይ መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ በፍርዱ በተለዩት ነጥቦች ላይ አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩን ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡ በዚህ መሰረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ክርክሩን በመስማት ላይ እያለ የአሁኗ 1ኛ አመልካች ቤቱን ከ2ኛ አመልካች ገዝታ ባለቤት የሆነችበት መሆኗን ጠቅሳ በቤቱ ላይ የተሰጠ ውሳኔ እንዲሰረዝላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡ ፍርድ ቤቱም በዚህ መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በተጠሪዎች መካከል የተደረገ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 204030 ላይ ለሰጠው ውሳኔ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪዎች በ2ኛ አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን፣ የክሱ ይዘትም የአሁን 2ኛ አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻነት አቶ ፈይሳ ጉዮ የተባለ ግለሰብ በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተመለከተውን ቤት ለ2ኛ አመልካች እንዲያስረክብ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68979 ላይ መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ይሰረዝልን የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በሌላ መዝገብ ላይ የተሰጠ ውሳኔ እንዲሰረዝ የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የለውም በሚል ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ፣ ሰበር ሰሚው ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 104920 ላይ መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡ ይህን ተከትሎም ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ የአሁን ተጠሪዎች መብት ያላቸው ስለመሆኑ በመ/ቁጥር 00867 ላይ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ 2ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት ወስኗል፡፡

4. አመልካቾች በሁለቱም መዛግብት ላይ በተሰጡት ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት በሁለቱም መዝገቦች ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካቾች ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፣ አቤቱታው ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች

በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ጥር 23 ቀን 2015 ዓ/ም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ውሳኔዉ እንዲጸናላቸዉ ተከራክረዋል፤ አመልካቾች በሰጡት የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

5. በአጭሩ ከላይ ከተመለከተው የክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ የሚቻለው ቁጥሩ 033 ሆኖ በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 15 ውስጥ የሚገኘውን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አስመልክቶ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ2ኛ አመልካች እና አቶ ፈይሳ ጉዬ በተባሉ ግለሰብ መካከል ክርክር ተደርጎ በመ/ቁጥር 68979 ላይ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ፈይሳ ጉዬ ቤቱን ለአሁን 2ኛ አመልካች እንዲያስረክቡ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 98979 2ኛ አመልካች ቤቱን መረከባቸው ተረጋግጧል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ተጠሪዎች በመ/ቁጥር 204030 በሆነው መዝገብ ላይ ላቀረቡት ክስ መሰረት ያደረጉት ይዜው ውሳኔ እንዲሰረዝላቸው ነው፡፡ በመ/ቁጥር 00867 ላይ የተሰጠ ውሳኔም ቢሆን በመ/ቁጥር 68979 ላይ ለ2ኛ አመልካች ተወስኖ በአፈፃፀም በእጁ የገባውን ቤት የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ በሆኑት ሁለቱ መዛግብት ላይ የተሠጡት ውሳኔዎች በውጤት ደረጃ በሌላ መዝገብ (መ/ቁጥር 68979) ላይ የ2ኛ አመልካች መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠን ውሳኔ የመሻር ውጤት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

6. ይህ በመሆኑም በአንድ መዝገብ ላይ የተሰጠ ውሳኔ እንዲሠረዝ በሌላ መዝገብ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ እንዲሁም በአንድ መዝገብ ላይ በተደረገ ክርክር የተሰጠን ዉሳኔ እና በአፈጻጸም ያለቀን ጉዳይ ውጤት አልባ የማድረግ ውጤት የሚያስከትል ክርክር በሌላ መዝገብ ላይ አስተናግዶ መወሰን ሥነ ሥርዓታዊ መሆን አለመሆኑ የዚህን ችሎት እልባት የሚያሻ ጭብጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተያዙ ሁለት አቋሞች ይስተዋላሉ፡፡ አንደኛው አቋም በሰ/መ/ቁጥር 50835 (ቅፅ 12 ላይ በታተመው) ላይ የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ነው፡፡ በዚህ መዝገብ ላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ፣ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀፅ 421 እና 455 ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በዋቢነት በመጥቀስ የያዘው አቋም በአንድ መዝገብ ላይ የተሠጠ ውሳኔ ከተፈፀመ በኋላም ቢሆን በውሳኔው መብቱ የተነካበት 3ኛ ወገን በሌላ መዝገብ ላይ ክስ አቅርቦ መብቱን ማስከበር ይችላል የሚል ነው፡፡

7. ሁለተኛው የችሎቱ አቋም በሰ/መ/ ቁጥር 67127 (በቅፅ 13 ላይ የታተመው) ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ የተንፀባረቀው ነው፡፡ በዚህ ዉሳኔ ችሎቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 358 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ በዚህ መዝገብ ላይ በሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መብቱን ይነካል የሚል ሰው በዚያው መዝገብ ላይ የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ መብቱን ማስከበር ከሚችል በቀር ዉሳኔዉ በአፈጻጸሙ ከተቋጨ በኋላ በሌላ መዝገብ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም፤ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የቀረበ ክስ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠትም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ከላይ በተመለከቱት ሁለቱ መዛግብት ላይ ለተሰጡ ውሳኔዎች መነሻ

የሆኑት በፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ መሠረት በአፈፃፀም በእጅ የገባውን ንብረት በሌላ ክስ ለማስመለስ በሶስተኛ ወገን የቀረበ ክስ ከመሆኑ አንጻር ሰበር ሰሚ ችሎቱ በተመሣሣይ ጉዳዮች በተለያየ አቋም ይሂል ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

8. ጉዳዩ ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ መዝገቡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 27(1/2) እንዲሁም በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 14 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ቀርቦዋል፡፡ በዚህ ችሎት እልባት የሚሻው ነጥብ ከላይ ከተጠቀሱት የሚቃረኑ አስገዳጅ ውሳኔዎች ገዢ መሆን ያለበትን ውሳኔ መለየት ሲሆን ይህ ችሎት ተሰይሞ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

9. በሁለቱ መዝገቦች የታዩት አቋሞች በአንድ በኩል ውጤታማ የሆነ የፍትሐብሔር ፍትህ ሂደት፣ ተገማች የሆነ ስርዓትና የዳኝነት ተቋሙን ወጥነት እንዲሁም ጉዳዮች የመጨረሻ እልባት ሊያገኙ የሚገባ መሆኑን ግብ ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ተገቢው ሥነ ሥርዓታዊ ሂደት መጠበቁን፣ በቂ ማስታወቂያ መሰጠቱንና ሰዎች መሰማታቸውን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በሁለቱ አቋሞች የሚጠበቁት እሴቶችና መብቶች መካከል ያለው ውጥረት ሕጎች ሲቀረጹ ሚዛን ለመጠበቅ ጥረት የሚደረግባቸው ሲሆን ውጥረቱ ግን ቀጣይ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳዮች ሂደት ሥነ ሥርዓት ሕጉ እነዚህን ተገዳዳሪ ፍላጎቶችን ለማስታረቅ ጥረት ያደርጋል፡፡ በአንድ በኩል መብቶች ተገቢው ዕድል ባልተሰጠበት ሁኔታ እንዳይወሰዱ ማረጋገጥ በሌላ በኩል ሂደቱ ውጤታማና ገደብ ያለው ካልሆነ ስርዓቱ ላይ የሚያስከተለውን አደጋ፣ መዘግየትና ወጪ ከግምት በማስገባት ሂደቱን ሚዛናዊ ለማድረግ፣ ለማፋጠን፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች እና ሕጉ እነዚህን ፍላጎቶች ለማስተናገድ ያደረገው መከራ እና ትኩረት የሕጉን ይዘት ይወስነዋል፡፡ ሕጎችም ይህን ሚዛን ለመጠበቅ የተያዘውን የፖሊሲ አቋም ያንጸባርቃሉ፡፡

10. በሁለቱ መዝገቦች በተያዙት አቋሞች ውስጥ በሚታየው ቅራኔ ተገዳዳሪ የሆኑ መርሆዎች መኖራቸውን በመዝገቦቹ ከተሰጠው ትንታኔ መረዳት ይቻላል፡፡ በውሳኔዎቹ የቀረቡት ትንታኔዎችና የተጠቀሱት መርሆዎች በራሳቸው ዋጋ ያላቸው ቢሆኑም ከአጠቃላይ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መንፈስና ግብ እንዲሁም አግባብ ባለው ድንጋጌ አንጻር ሲታዩ የሚኖራቸውን ውጤት መፈተሽ ተገቢ ከመሆኑም በላይ ከሕጉ ይዘት በመነሳት ወጥ የሆነ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት ሕጉ በግልጽ የደነገገውን እንዲሁም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መመርምር አስፈላጊ ነው፡፡

11. እንደሚታወቀዉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ በመምራት ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማስቻል ነዉ፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተለያዩ ደንቦች እና መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡ ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለዉ ሁኔታ እንዲመሩ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን፣ ብሎም ክርክሮች ባነሰ ወጪ እና ጊዜ መቋጫ እንዲያገኙ

በማድረግ በፍርድ ቤት እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ ያላግባብ የሚደርሰዉን የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት በማስቀረት የክርክሩ ሂደትም ሆነ ዉጤቱ ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የሚኖረዉ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በህጉ ላይ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲዉሉ የማድረጉ አስፈላጊነትም የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

12. የሥነ ሥርዓት ሕግ ሰዎች የመሰማት መብት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተገቢውን ሥነ ሥርዓታዊ መሳሪያዎችን ያካተተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው መሰረታዊው መርህ አንድ ውሳኔ አስገዳጅ የሚሆነው በተከራካሪ ወገኖች ላይ ሆኖ የሚበይነውም በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለውን የመብትና ግዴታ ግንኙነት ነው የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ውጤት የሚኖረው በተከራካሪ ወገኖችና በነሱ ስር መብት በሚጠይቁት ላይ ሲሆን ለጉዳዩ እንግዳ የሆኑ ሰዎችን አይመለከትም የሚለው መርህ አጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘ ነው፡፡ ይህን በመከተል በተከራካሪ ወገኖች መካከል በተደረገ ክርክር የተሰጠ ውሳኔ ሌሎች ለጉዳዩ እንግዳ የሆኑ ሰዎችን አይጎዳም ወይም አይጠቅምም (the principle of *res inter alios judicata*, i.e., a matter judged between others) የሚለው መሰረታዊ መርህ ነው፡፡ ይህ ደንብ የአገሮችም ሆነ በአለም አቀፍ ሕጎች በስፋት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን በበርካታ አገር ሕጎች እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ ለአብነት ሊጠቀስ በሚችለው የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሕግ አንቀጽ 59 በግልጽ ተካቶ መገኘቱ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

13. ይህ ጽንሰ ሐሳብ በኢትዮጵያ ሕግም በግልጽና በቀጥታ ባይጠቀስም እውቅና ያለው ለመሆኑ በዋናነት ዋቢ የሚሆነው የሕግ መነሻ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ጉዳይ አስቀድሞ ተወስኗል ተብሎ መቃወሚያ እንዲሆን መሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ የተከራካሪ ወገኖች አንድ መሆን ነው፡፡ በውጤቱም ተከራካሪዎቹ አንድ ካልሆኑ ማለትም በጉዳዩ ከተሰየሙት ወይም በነሱ ስር ሆነው መብት ከሚጠይቁ ውጭ ያሉ ሰዎች ውሳኔው በሚመለከተው ጉዳይ አዲስ ክስ ከማቅረብ አይከለከሉም፡፡ ይህ ድንጋጌም ለፍርድ የአስገዳጅነት ውጤት የሰጠው በተከራካሪ ወገኖችና በነሱ ስር መብት ባገኙት ወገኖች መካከል ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ለተፈጻሚነቱ መሟላት ካለባቸው መስፈርቶች አንዱ የሆነው የተከራካሪ ወገኖችን ተመሳሳይነት በተመለከተ ልዩ ሁኔታዎችን የማያስተናግድ ፍጹም የሆነ ደንብ አይደለም፡፡ ለማሳያነት ያህልም ድንጋጌውን የያዘውና መርዑን ያስተዋወቀው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 በንዑስ አንቀጽ 4 ልዩ ሁኔታ ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መሰረት ብዙ ሰዎች ክስ አቅርበው በቅን ልቦና የተከራከሩ እንደሆነ በመብቱ አግባብ ላላቸው ሌሎች ሰዎች በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ ቢቀሩም እንኳ ተከራካሪ ከነበሩት ሰዎች መብት እንዳገኙ እንደሚቆጠር ደንግጓል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተከራካሪ ሆነው ያልተሰየሙ ነገር ግን በበቂ ሁኔታ ተወክለዋል ብሎ ሕጉ በማመኑ ሰዎች ባልተከረካሩበት መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ እንዲያስገድዳቸው ተደርጎዋል፡፡ በሕጎች፣ በሕግ አስተምህሮም ሆነ

በሌሎች አገራት የታወቁ ልዩ ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን በዋናነት ከላይ የተጠቀሱትን የሚጋጩ ግቦችን ማስታረቅ እና የሂደቱን ውጤታማነት እና ወጪ ቆጣቢ መሆንን ግብ ያደረጉ ናቸው፡፡

14. በዚህ መሰረት የየአገሩ ሕግ አጠቃላይ ማዕቀፍ፣ የፖሊሲ መደላድል፣ የሕጉን ግብና ትኩረት መሰረት አድርጎ ከላይ ለተመለከተው አጠቃላይ መርህ የሚቀበላቸው ልዩ ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን በዋናነት የሚጠቀሰው ሁሉንም የሚያስገድዱ ውሳኔዎች (*in rem* judgments) እውቅና የሚሰጠው መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ የቀረበው መርህ አጠቃላይ ተቀባይነት እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔ በሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚኖረውን ውጤት በፍርዶች ዓይነት ሊበየን ይችላል፡፡ ውሳኔዎች ግላዊ (*in personam*) ወይም ሁሉን አስገዳጅ (*in rem*) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአጭር አገላለጽ የመጀመሪያው በግለሰቦች መካከል ባለ የመብት ክርክር ላይ የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው በንብረት ወይም በሕጋዊ አቋም (status) ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ነው፡፡ የመጀመሪያው በግለሰብ ላይ የሚቀርብ እና ተከራካሪ ወገኖችን ብቻ የሚያስገድድ ሲሆን ሁለተኛው ግን በንብረት ላይ የሚቀርብና በውጤቱም በመላው አለም ላይ የሚሰጥ ሁሉንም ሰዉ የሚያስገድድ ነው፡፡ ሁሉን አስገዳጅ ፍርድ ‘አንድ ፍርድ ውጤት የሚኖረው በተከራካሪ ወገኖች ላይ ብቻ ነው’ በሚለው መርህ የማይገዛ ልዩ ሁኔታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህን የውሳኔዎች የዓይነት ድልድል ተከትሎ የሚቀርበው ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕግ ለዚህ ዓይነት ምደባ እውቅና የሚሰጥና ይህን መሰረት አድርጎ የውሳኔዎችን ተፈጻሚነት ልዩነት የሚያደርግ ስለመሆኑ ማጣራትን የግድ ይላል፡፡

15. ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው በፍርዶች መካከል የዚህ ዓይነት ክፍፍል አልተደረገም፡፡ የሕግ አቋም (status) ለማረጋገጥ (የመክሰር ውሳኔ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ወራሽነት ወዘተ) የሚቀርቡ ማመልከቻዎች እና በዚህ ላይ ተመስርተው የሚሰጡ ሁሉንም የሚያስገድዱ ውሳኔዎች ለዚህ ማሳያ ሆነው የሚጠቀሱ ሲሆን የኢትዮጵያ ሕግ ፍንጭ ሰጪ ከሆኑ ድንጋጌዎች ባለፈ በግልጽ እውቅና አለመስጠቱ ብቻ ሳይሆን ሥነ ሥርዓት ዘርግቶ ልዩነት የሚፈጥሩትን ሂደቶችና ይህን ተከትሎ የሚገኘውን ውጤት የሚገዛ ዝርዝር ድንጋጌ አልያዘም፡፡ ሕጉ የሚያውቀው ውሳኔ ወይም ፍርድ አንድ ዓይነት ብቻ በመሆኑ የተጠቀሰውን ውጤት ለማምጣት የሚያስችል እውቅና ለክፍፍሉ በግልጽ ተሰጥቷል የሚያስብል ይዘት የለውም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሕጋዊ አቋምን በተመለከተ የሚሰጡ ውሳኔዎች ሁሉንም ሊያስገድዱ ይችላሉ የሚል ማጠቃለያ ለመድረስ የሚያስችሉ ዉሳኔዎችን አልሰጠም፡፡

16. የሌሎች አገሮችን ልምድ ስናይ ሁሉን የሚያስገድዱ ውሳኔዎች መነሻ መሰረታዊ ሕግ፣ የሥነ ሥርዓት ሕግ ወይም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሆነው እናገኛለን፡፡ የዚህ ዓይነት ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ውሳኔዎች በጉዳዩ ዓይነት ለይተው በሕግ ከደነገጉ አገራት መጠቀስ የምትችለው የኢትየጵያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምንጭ ተደርጋ የምትወሰደው ሕንድ፣ የማስረጃ ሕግ (the Indian Evidence Act) ሁሉንም የሚያስገድዱ ውሳኔዎችን ለይቶ ያመለክታል፡፡ የሕጉ አንቀጽ 41 ኑዛዜን፣ የጋብቻ ሁኔታ፣መክሰር እና በባህር ህግ መሰረት የሚቀርቡ የይገባኛል

ጥያቄዎች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ ድምዳሜ የያዙ ማስረጃ ተደርገው እንደሚወሰዱ ይደነግጋል፡፡

17. ከሥነ ሥርዓት ሕግ አኳያ ሁሉንም የሚያስገድዱ ፍርዶች በተነጻጻሪ ያሉ መብቶች መጣስን እንዳያስከትሉና የሚሰጠው ውሳኔም ተፈጻሚ ሆኖ የሚፈለገውን ውጤታማነት ለማሳካት የመጥሪያ አደራረስን በተመለከተ የተለየ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ ውሳኔዎች አስገዳጅነትን ለማስፋት አንዱ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የመጥሪያ አደራረስ ስርዓቱ በመዝገቡ ለተሰየሙት ብቻ ሳይሆን በክርክሩ ጥቅም ላላቸው ሰዎች መጥሪያ እንዲደደርስ በማድረግ በውሳኔው እንዲገደዱ ይደረጋል፡፡ ንብረትን የተመለከተ ጉዳይ የሚያይ ፍርድ ቤት ንብረቱን በተመለከተ ያለውን ክስ ለሌሎች ወገኖች የሚያሳውቅበት (*lis pendens* notice) ሥርዓት እውቅና የሚሰጡ አገሮች አሉ፡፡ የዚህ ማስታወቂያ የሕግ ውጤት በንብረቱ ላይ መብት የሚያገኙ ሰዎች በሚሰጠው ውሳኔ የሚገደዱ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ማስታወቂያ ባልተሰጠበት በቅን ልቦና ክርክሩ በሚመለከተው ንብረት ላይ ከክሱ መመስረት በኃላ መብት ያገኙ ሰዎች ስለጉዳዩ መኖሩ ባላወቁበት ሁኔታ በውሳኔው የሚገደዱበት አግባብ ጥያቄ የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

18. ከላይ ለማሳያነት ከቀረቡት ሥነ ስርዓታዊ መጠበቂያዎች ውጭ ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ተፈጻሚነት ወሰንን ለማስፋት ሌሎች መመዘናዎች ይጠቀማሉ፡፡ አንደኛው በእኛም ሕግ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(4) እንደተመለከተው አንድ ሰው ጥቅሙ በክርክሩ በበቂ ሁኔታ ተወክሏል ተብሎ ሲታመን ነው፡፡ ይህ በዚህ ድንጋጌ የተካተተው ሐሳብ በድንጋጌው ከተገለጸው ሁኔታ ውጭም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በቀደመው ክርክር ተሳታፊ ባይሆንም ጥቅሙ በቀድሞው ክርክር በበቂ ሁኔታ ተወክሎ ከነበረ በውሳኔው እንዲገደድ ይደረጋል፡፡ ይህ ምናባዊ ውክልና (virtual representation doctrine) በመባል የሚታወቀው ጽንሰ ሐሳብ ተከራካሪ ወገኖች ያልሆኑ ሰዎች በውሳኔ የሚገደዱበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ ሕጻናት በጽንስ እያሉ በሚካሄድ ክርክር ጥቅማቸው እንደተወከለ በመቀበል በውጤቱ እንዲገደዱ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ክርክሩን የመሩና በፋይናንስ የደገፉ ሰዎች ተከራካሪ ባይሆኑም በውሳኔው እንዲገደዱ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ የአንድ ውሳኔ አስገዳጅነት ከተሰየመው ተከራካሪ ወገን ወይም በሱ ስር የሚጠይቁትን ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ ግንኙነት ያላቸውንና ከዚህም አልፎ ጥቅማቸው በበቂ ሁኔታ የተወከሉትን እና ክርክራቸው በአግባቡ ቀርቦ የተወሰኑትን እንዲጨምር የማድረግ ዝንባሌ በብዙ አገሮች ይስተዋላል፡፡

19. የኢትዮጵያ ሕግን ስናይ በፍርዶች መካከል ክፍፍል የማያደርግ ከመሆኑም በላይ የውሳኔዎችን የተፈጻሚነት ወሰን ለማስፋት የሚያስችሉ የተለያዩ ሥነ ስርዓታዊ መሳሪያዎችን አይጠቀምም፡፡ በርግጥ አንድ ሰው ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል የሚሰጥ ውሳኔ በውሳኔው ባለዕዳ የተደረገውን ሰው ብቻ የሚመለከት ግለሰባዊ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ንብረትን ወይም ሕጋዊ አቋምን በተመለከተ የሚሰጡ ውሳኔዎች ከተከራካሪ ወገኖች አልፈው ሌሎች ሰዎችን ማስገደድ እንዲችሉ ተገቢው ሥነ ሥርዓዊ ማዕቀፍ መኖሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ አጠቃላይ የፍትሐብሔር ሥነ

ሥርዓት ሕጉን መንፈስ እና ማዕቀፉ ተቃራኒ የሆኑትን ፍላጎቶች በምን መልክ ምላሽ እንደሰጠ ማየት ይረዳል።

20. አንድ ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ክርክር መካሄድን ለማስቀረትና ጉዳዩች በአጭር ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሂደት እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ሕጉ ሁሉም ባለድርሻዎች ይህን ግብ ለማሳካት ያለባቸውን ኃላፊነታት እንዲወጡ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ሞክሯል። ከሳሽ የሚወሰነው የሕግ ጥያቄና የስረ ነገር ጭብጥ አንድ ሊሆን በሚችል ጊዜ ተከሳሾችን በአንድነት አጣምሮ እንዲከስ (አንቀጽ 36)፣ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ወገኖች ወደ ክርክሩ መጥራት እንዲችል (አንቀጽ 40(2))፣ ተከራከሪ ወገን ግዴታ የሚጋራውን ወገን ወደ ክርክሩ ስቦ እንዲያስገባ (አንቀጽ 43)፣ እንዲሁም ስለክርክሩ መኖር ያወቁ ጥቅም ያላቸው ሰዎች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ (አንቀጽ 41) የሚያስችሉ ሥነ ሥርዓታዊ መንገድ ተመቻችቷል። በፍርድ ቤቱም ሆነ በተከራካሪ ወገኖች የሚመለከታቸው ሰዎች በክርክሩ ተካተው ውሳኔ እንዲሰጥ የተደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ ውጤታማ ውሳኔ እንዲሰጥ ለማድረግም ሕጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን ይዞዋል። ተከራካሪዎችን ስለማጣመር በሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ክፍል በአንቀጽ 36(3) በርካታ ንብረት ጠባቂዎች፣ ንብረት አስተዳደሪዎች፣ ኑዛዜ አስፈጻሚዎች ንብረት አስተዳዳሪዎች በሚኖሩበት ጊዜ የሚጠብቁትን ንብረት በተመለከተ በአንዱ ላይ የሚቀርበው ክስ ሌሎቹም ተከሳሽ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስለቀቅ የሚቀርብ ክስ በንብረቱ ላይ ሰፍረው የሚገኙትን ሁሉ አጣምሮ መክሰስ እንደሚገባ አንቀጽ 36(4) ደንግጎዋል። ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች በጥብቅ ከተተገበሩ ሁሉን አካታች እና ውጤታማ ውሳኔ ስለሚሰጥ በዚሁ ጉዳይ የአዲስ ክስ የሚነሳበት እድል የለም ወይም አነስተኛ ነው። ጥያቄ የሚሆነው በተለያየ ምክንያት ይህ ሳይፈጸም ፍርድ ቢሰጥ በከሳሽ ወይም በፍርድ ቤት እንዲካተቱ ያልተደረጉ ጥቅም ያላቸው ሰዎች በፍርዱ መገደድ መቻላቸው ነዉ።

21. ከዚህ በላይ ከቀረበው አንጻር አንድ ዉሳኔ የክርክሩ ተሳታፊ ከሆነዉ ወይም መብቱ ከሚተላለፍለት ሰዉ ወይም በክርክሩ እንደተወከለ ከሚቆጠር ሰዉ ዉጪ በሆነ ሰዉ ላይ አስገዳጅነት ለማድረግ የሚያስችል የተዘጋጀ የሕግ ምላሽ እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ማለት ግን የሕጉ ይዘት ዉሳኔዉ የሦስተኛ ወገንን መብት በፍጹም ሊነካ የሚችል ዉጤት አያስከትልም ለማለት የሚያስችል አይደለም። በሌላ አነጋገር በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል በተደረገ ክርክር መነሻነት የሚሰጥ ዉሳኔ የክርክሩ አካል ያልነበረን የሦስተኛ ወገን መብት/ጥቅም ሊነካ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። ይህን እዉነታ ከግምት ዉስጥ በማስገባትም ከላይ እንዳየነው በክርክሩ በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ተከራካሪዎች ዉጭ ያለ ሌላ ሦስተኛ ወገን የክርክር ተሳታፊ ሊሆን የሚችልበትን ሥነ ሥርዓት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተዘርግቷል። ክርክሩ ካለበት ደረጃ አንፃር ሦስተኛ ወገን ወደ ክርክር እንዲገባ የሚደረግባቸዉ ሁኔታዎች ሁለት ገጽታዎች አሉት። የመጀመሪያዉ ዉሳኔ

ከመሰጠቱ በፊት ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ የሚመለከተው ሰው ወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚደረግበት ሥርዓት ነዉ፡፡ ሁለተኛው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሚቀርብ አቤታተ የሚስተናገድበት ሥርዓት ነው፡፡

22. የመጀመሪያውን ስናይ ሦስተኛ ወገን ወደ ክርክር እንዲገባ የሚደረገዉ አንድም ዉጤቱ መብቴን ሊነካ ይችላል በሚል ወገን (*interested party*) አቤቱታ ሲቀርብ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ለክርክሩ አስፈላጊ እና አግባብነት ያለው ሰው (*necessary party*) መሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት የክርክር ተሳታፊ የሚሆንበትን ሥርዓት ነዉ፡፡ አስፈላጊ አግባብ ያለው ሰው (necessary party) በሌሎች የኮመን ሎው ስርዓት በሚከተሉ አገሮች አቻው የሚሆነው '*indispensable party*' የሚለው ሐረግ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ምንጭ ተደርጎ በሚወሰደው የሕንድ ሕግ ያለውን ትርጉም ስንወስድ ያለዚህ ሰው ተሳትፎ ፍርድ ቤት በሕጋዊ መንገድ ክርክሩን መቋጨትም ሆነ ውጤታማ ትህዛዝ መስጠት አይቻልም፡፡ የዚህ አስፈላጊ ወገን በክርክሩ የመሳተፉ ፋይዳ የተሟላ፣ ሁሉን አቀፍና ውጤታማ ውሳኔ በመስጠት በተመሳሳይ ጉዳይ ተደጋጋሚ ክሶችን መመስረትን ለማስወገድ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ የሆነ አግባብ ያለው ሰው ባልተካተተበት ሁኔታ የሚሰጠው ውሳኔ የማያስገድዳቸው ሰዎች እንዲኖሩ ስለሚያደርግ የመጨረሻና ውጤታማ ውሳኔ ማሳለፍ እንዳይችል ያደርገዋል፡፡

23. በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 የተመለከተው እየታየ ባለው ጉዳይ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሶስተኛ ወገን ከፍርድ በፊት ጣልቃ ገብ ሆኖ መከራከር እንደሚችል የሚፈቅድ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ ከሚታየው ነጥብ አንጻር ድንጋጌው ፈቃጅ በመሆኑ በዚህ መብት እያወቀ ያልተጠቀመ ወገን ላይ የሚኖረው ውጤት ማየቱ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ከታች በተራ ቁጥር 25 በዝርዝር በቀረበው የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው አስገዳጅ ትርጉም ለዚህም አግባብነት ያለው አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ በተለይም በሰ/መ/ቁ. 56795 (ቅጽ 12) ፍርድ ቤቱ በትንታኔው *"በማንኛውም ጉዳይ ቢሆን በአንድ ጉዳይ ላይ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔ በኋላ የመሟገት መብት አለው በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሔ/ቁ. 358 የተለጠጠ ትርጉም ለመስጠት ተፈልጎ አይደለም፡"*ብሎዋል፡፡ ከዚህም በላይ ጣልቃ እንዲገባ ተፈቅዶለት መጥሪያ ያላደረሰ አመልካች መብቱ እንደሚሰረዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41(4) መመልከቱ እንዳለ ሆኖ በዚህ ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት እንደሌለው ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 40229 (ቅጽ 9) አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሁለቱ ድንጋጌዎች (የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 እና 358) አማራጭ አለመሆናቸውና ጣልቃ መግባት እየቻለ በዚህ መብት ያልተጠቀመ ወገን በቀጣይ ባለው ሂደት ያሉ መፍትሔዎችን መጠቀም እንደማይችል አመላካች ነው፡፡

24. ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔው ጥቅሜን ይነካል የሚል ሶስተኛ ወገን ያለው መፍትሔ ሁለተኛዉ ገጽታ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ድንጋጌ ላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ ታሳቢ የሚያደርገዉ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ በክርክሩ ተሳታፊ ሆኖ መብቱን ማስከበር ይችል

የነበረ ሰዉ ተሳታፊ ባልሆነበት ክርክር መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ነዉ፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጠ ዉሳኔ መብቱ ተነክቷል የሚል ሦስተኛ ወገን አቤቱታዉን አቅርቦ ዉሳኔዉን በመቃወም መብቱን ማስከበር ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረዉ ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት የቀረበ እንደሆነ ሲሆን፣ የመቃወም አቤቱታዉ ተቀባይነት ካገኘም ክርክሩ በአዲስ መልክ (የመጀመሪያዉ ክርክር በተሰማበት ሥርዓት) የሚመራ ስለመሆኑም ከህጉ አንቀጽ 360(2) ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከህጉ አንቀጽ 358 ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘ ከሚነሱት አከራካሪ ነጥቦች ዉስጥ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያላቸዉን የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ማየት ያስፈልጋል፡፡

25. የመጀመሪያ አከራካሪ ነጥብ ስለ ክርክሩ ባለማወቅ ወይም በቸልተኝነት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ወደ ክርክሩ ገብቶ መብቱን ያላስከበረ ሰዉ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነገር ግን ከአፈፃፀም በፊት በህጉ አንቀጽ 358 የሚያቀርበዉ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነትን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ድንጋጌዉ በግልጽ የሚለዉ ነገር ባይኖርም፣ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ስለ ክርክሩ መኖሩንና ዉጤቱም መብቱን ሊነካ እንደሚችል እያወቀ ወይም በቸልተኝነት ዉሳኔዉ ከመፈጸሙ በፊት የመቃወም አቤቱታ ቢያቀርብም አቤቱታዉ ተቀባይነት ሊኖረዉ እንደማይገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ/መ/ቁጥር በሰ/መ/ቁ. 40229፣ 93998፣181236 ጨምሮ በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ ገዥ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ ሁኔታ አቋም የተያዘበት ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብት ይጥሳል በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥ የቀረበለት የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ6ኛ ዓመት የፓርላማ ዘመን 3ኛ የስራ ዓመት 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም በመ/ቁ 122/16 በሰጠው ውሳኔ ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ የሰጡት ሕግ ተርጉመው በመሆኑና ሕግ የመተርጎም ስልጣን የፍርድ ቤቶች ነው በማለት የሰበር ሰሚ ችሎቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት በመ/ቁ. 210077 የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ክርክሩ ስለመኖሩ እያወቀ በቸልተኝነቱ የክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የቀረ ሦስተኛ ወገን ዉሳኔ ከመፈጸሙ በፊት የመቃወም አቤቱታ ቢያቀርብ ተቀባይነት የሌለዉ ሲሆን፤ በአንፃሩ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ያልተሳተፈዉ ክርክሩን ባለማወቅ ወይም በራሱ ቸልተኝነት ባልሆነ ሁኔታ ከሆነ መቃወሚያዉ ተቀባይነት ያለዉ ስለመሆኑ እልባት ተሰጥቶት የሚገኝ ጉዳይ መሆኑን፡፡

26. ሁለተኛዉ አከራካሪ ነጥብ ክርክሩ በሂደት ላይ ስለመሆኑ እያወቀ በራሱ ቸልተኝነት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጣልቃ ገብቶ መብቱን ያላስከበረ ሰዉ ፍርዱ ከተፈጸመ በኋላ የሚያቀርበዉ የመብት ጥያቄ የሚስተናገድበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ የሚቀርበዉ የተሰጠ ዉሳኔ ከመፈጸሙ በፊት ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሕግ አዉጪዉ ሦስተኛ ወገን የመቃወም አቤቱታ የሚያቀርብበትን ሁኔታ በጊዜ ሳይገድብ ከአፈፃጸም በፊት በማንኛዉም ጊዜ

ማቅረብ እንደሚችል የደነገገዉ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ወይም ከዉሳኔ በኋላም ቢሆን መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ስለመሰጠቱ ሊያዉቅ የማይችልበት ሁኔታ ቢኖርም፣ በአፈፃፀም ጊዜ መብቱን የሚነካ ዉሳኔ መኖሩን ማወቅ የሚችልበት ዕድል ከፍተኛ መሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንደሆነ ይታመናል። የክርክሩ ተሳታፊዎች በሚፈጽሙት ያልተገባ ተግባር ወይም ከአቅም በላይ ወይም በሌላ ምክንያት መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ስለመኖሩ ባለማወቁ ዉሳኔዉ ከመፈጸሙ በፊት ሦስተኛ ወገን አቤቱታ ላያቀርብ የሚችልባቸዉ ሁኔታዎች እንዳሉ ይታመናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ድንጋጌዉ በግልጽ የሚለዉ ነገር የሌለ ሲሆን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢዉ ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ስለ ክርክሩ ወይም የክርክሩ ዉጤት መብቱን ሊነካ የሚችል መሆኑን እያወቀ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ያላስከበረ ሰዉ በእራሱ ቸልተኝነት መሆኑ ከታወቀ የመቃወም አቤቱታዉ ተቀባይነት እንደሌለዉ ለሰጣቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች መሠረት ያደረገዉ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት የቀረበዉን የመቃወም አቤቱታ በመሆኑ ለዚህ አከራካሪ ነጥብ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም።

27. በመሆኑም ፍርድ ከተፈጸመ በኋላ ያንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በሌላ መዝገብ ላይ አዲስ ክስ ሊቀርብ የሚችልበት ሕጋዊ መሰረት መኖር አለመኖሩ መመርመር ያለበት ነጥብ ነዉ። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 50835 (ቅፅ 12 ላይ በታተመው) ላይ በሰጠዉ ትርጉም አዲስ ክስ ማቅረብ ይቻላል በሚል ለያዘዉ አቋም በዋቢነት የጠቀሰዉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 418፣ አንቀፅ 421 እና አንቀጽ 455 ድንጋጌዎችን ነዉ። በርግጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 የአንድ ንብረት መከበር ወይም መያዝ በመቃወም አቤቱታ ያቀረበ ሰው አቤቱታውን ባለመቀበል ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ ክስ ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል። ይሁንና ለዚህ ድንጋጌ መነሻው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ከተደረገ የሚኖር መፍትሔ ነው። የንብረት ማስከበርና መያዝ ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠ ውሳኔን ለማስፈጸም የሚከናወን መሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 394 መረዳት ይቻላል። የንብረት መያዝ ወይም መከበር ዓላማ በፍርድ የተረጋገጠ ገንዘብ ለማስከፈል በመሆኑ ንብረቱ በውሳኔ በተጠናቀቀው ጉዳይ አከራካሪ የነበረ አይደለም። ስለዚህ የቀረበው ተቃውሞ የሚፈጸመውን ውሳኔ በቀጥታ የማይመለከት ከመሆኑም በላይ የንብረቱ መያዝ ወይም መከበር ፍርድ ያረፈበትን የገንዘብ መጠን ለማስከፈል ዓላማ ስለሆነ ከሚፈጸመው ውሳኔ አንጻር አዲስ ወይም ተቃራኒ ውሳኔ አያስከትልም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 53607 ላይ በሰጠዉ ትርጉም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ መሰረት በዋናው ክርክር መነሻነት የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ወይም የሚያሻሽል ውሳኔ እንደማይሰጥ በማስረገጥ የዚህ ዓይነት ውሳኔ መስጠት የሚቻለው የመቃወም አቤቱታ (የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358) ሲቀርብ ነው ብሏል። ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ የተጠቀሰው አዲስ ክስ ከዋናው ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ባለመሆኑ በዚህ

መዝገብ ከሚታየው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌለውና ጸንቶ ያለን ውሳኔ የሚገዳደር ውሳኔ ለማሰጠት የሚመሰረት ክስ ባለመሆኑ በዚህ መዝገብ ለሚታየው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡

28. የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 455 ድንጋጌን ስንመለከት፣ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 451፣ 452 እና 453(3) ድንጋጌዎች የሚንደረደር ሲሆን፤ እነዚህ ድንጋጌዎች የማይንቀሳቀስ ንብረት የፍርድ ባለመብት ወይም ገዥው ንብረቱን እንዳይረከብ የሚቃወም ሰዉ፣ ወይም በፍርድ ወይም በፍርድ ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት የለቀቀ ሰዉ ንብረቱን መልቀቁን በመቃወም ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ስለሚያቀርበት ሥርዓት የሚደነግጉ ናቸዉ፡፡ የሕጉ አንቀጽ 455 ድንጋጌ ደግሞ በዚህ አግባብ የቀረበ ማመልከቻ ዉድቅ የተደረገበት ሰዉ በንብረቱ ላይ መብት ያለዉ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ ፍርድ ሳያርፍበት በገንዘብ ዕዳ ምክንያት በአፈፃፀም የተያዘ ንብረትን ብቻ የሚመለከት ነዉ ወይስ ፍርድ ያረፈበትን ንብረት ጭምር ይመለከታል? የሚለዉ አከራካሪ ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ድንጋጌዉ ፍርድ ያረፈበትን ንብረት ጭምር ይመለከታል የሚባል ቢሆን እንኳን የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስረከብ መቃወምን መነሻ ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ያረፈባቸዉን ማናቸዉንም ጉዳዮች በሌላ መዝገብ ላይ አዲስ ክስ አቅርቦ መገዳደርን የሚፈቅድ ድንጋጌ ነዉ ብሎ መደምደም የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን አንቀጽ 455 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ፍርድ ያረፈበት አንድን ጉዳይ የሚገዳደር ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ ይቻላል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡

29. ይልቁንም በሌላ የፍርድ መዝገብ መብቱ ተነክቷል የሚል ሰዉ አዲስ ክስ አቅርቦ በሌላ መዝገብ ላይ መብቱን ማስከበር የሚችል መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን አንቀጽ 358 ድንጋጌ አጠቃላይ ዓላማ በአንድ በኩል፤ ፍትሕ የማግኘት መብትን በሌላ በኩል ሥነ ሥርዓታዊ ዉጤታማነትን (procedural efficiency) ከግምት ዉስጥ ማስገባት የግድ ይላል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ በኩል ክርክሮች ተጠቃለዉ በአንድ መዝገብ እንዲታዩ በማድረግ የክርክር ሂደቱ ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን እንዲሁም በአንድ ጉዳይ ላይ በርካታ መዛግብት ተከፍተዉ ለፍርድ ቤቶች ሊቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ በማስቀረት የዉሳኔዎችን ወጥነት እና ተገማችነት ማረጋገጥን፤ በሌላ በኩል ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ስለክርክሩ ባለማወቁ ወይም በሌላ ምክንያት ጣልቃ ገብቶ መብቱን ማስከበር ያልቻለ ወይም በማንኛዉም መልኩ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቱን የሚነካ ሰዉ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያ አቅርቦ መብቱን እንዲያስከብር በማድረግ የመሰማት መብትን ማረጋገጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም በተያዘዉ ጉዳይ ላይ የሚሰጥ ትርጉም በአንድ በኩል ሥነ ሥርዓታዊ ዉጤታማነትን (procedural efficiency) በሌላ በኩል ደግሞ ፍትሕ የማግኘት መብትን ያማከለ ሊሆን ይገባል፡፡

30. ከፍ ሲል በተራ ቁጥር 25 ላይ እንደተመለከተዉ፣ ተከራካሪ ባልሆነበት ክስ የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የነካ ሰዉ ክርክሩ በሂደት ባለበት ወቅትም ሆነ በአፈፃጸሙ ጊዜ ከአቅም በላይ በሆኑ

የተለያዩ ምክንያቶች መብቱን የሚነካ ውሳኔ ስለመኖሩ ላያዉቅ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። በዚህ ምክንያት መብቱን የሚነካ ውሳኔ ስለመሰጠቱ ከአፈፃፀም በኋላ ያወቀ ሰዉ አዲስ ክስ አቅርቦ መብቱን ማስከበር የሚችል መሆን አለመሆኑ ከአጠቃላይ ፍትሕ የማግኘት መብት ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት ነዉ። ፍትሕ የማግኘት መብት የግለሰቦች ነፃነትና ንብረት አደጋ ላይ ሲወድቅ ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ በፍትሐዊ እና ትክክለኛ የክርክር ሂደት መፍትሔ የማግኘት መብትን የሚመለከት ሲሆን፣ ከመሠረታዊ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ዉስጥ አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ነዉ። ይህ መብት ስለ ሰብአዊ መብቶች በሚደነግጉ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስነዶች የተደነገገ ሲሆን፣ የኢፌዲሪ ህገ መንግስትን በአንቀጽ 37(1) ድንጋጌዉ ዕዉቅና ሰጥቶታል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ስልጣን ወደ ተሰጠው አካል በማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል። ሰዎች በመካሄድ ላይ ያለ ክርክር በቂ ማስታወቂያ ሳይሰጣቸው፣ ሳይሰሙ፣ ማስረጃ ሳያቀርቡ በአጠቃላይ ፍርድ ቤት የመቅረብ እድል ሳያገኙ በሌሉበት የተሰጠ ፍርድ በቀጣይ ክስ አቅርበው መብታቸውን ለማስከበር ገደብ የሚሆንባቸው ከሆነ በሕግ የተረጋገጠው መብትም ሆነ ይህን መብት ለማስከበር የተቀመጠው ሥነ ሥርዓታዊ መፍትሔ ዋጋ ያጣል የሚል ነው።

31. ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ስለ ክርክሩ ባለማወቅ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወደ ክርክሩ መግባት ያልቻለ ሦስተኛ ወገን ከውሳኔዉ በኋላ ያልተሳተፈበትና የሚጎዳው ፍርድ መኖሩን ቢያውቅ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ ስለሚችል ሥነ ሥርዓታዊ መፍትሔ አለው። ይሁንና በተመሳሳይ ምክንያት ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት የክርክሩ ተካፋይ መሆን ሲገባዉ ተካፋይ ያልሆነ ሰዉ ወይም ዉሳኔዉ ከተፈጸመ በኋላ መብቱን የሚነካ ዉሳኔ መኖሩን ያወቀ ሰዉ መብቱን ማስከበር የሚችልበት የመብት ማስከበሪያ መንገድ አዲስ ክስ ማቅረብ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል በአንድ የክስ መዝገብ እልባት የተሰጠበት ጉዳይ በሌላ አዲስ መዝገብ ላይ ክርክር እንዲቀጥል ማድረግ ክርክሮች ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ እንዳይሆኑ ያደርጋል፤ በአንድ ጉዳይ ላይ በርካታ መዛግብት ተከፍተዉ ለፍርድ ቤት እንዲቀርቡ በር የሚከፍት ሲሆን፣ ይህ መሆኑ ደግሞ የዉሳኔዎችን ወጥነት እና ተገማችነትን ጥያቄ ዉስጥ ያስገባል። በዉጤቱም የፍትሐብሔር ክርክሮች ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ሂደቶቹም ሆነ ዉጤታቸዉ ወጥ እና ተገማች ማድረግ ነዉ የሚለዉን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መርህ እንደ አጠቃላይ፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 358 ድንጋጌን ዓላማ በተለይ ይገዳደራል።

32. በመሆኑም በተለያዩ ምክንያቶች የክርክር ተሳታፊ ሳይሆን የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካ ሰዉ መብቱን ለማስከበር ያለዉ የመጀመሪያዉ የመፍትሔ አማራጭ ዉሳኔዉ ከመፈጸሙ በፊት የመቃወም አቤቱታ በማቅረብ መብቱን ማስከበር ሲሆን፣ መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ስለመኖሩ

የሰ/መ/ቁ. 236212

ጥር 25 ቀን 2018 ዓ/ም

ያወቀዉ ዉሳኔዉ ከተፈጸመ በኋላ ከሆነ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል ቢሆንም፣ በዚህ ሁኔታ የሚያቀርበዉ ክስ ተቀባይነት የሚኖረዉ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለም ሆነ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ እስከሚፈጸም ድረስ መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ስለመኖሩ ላያዉቅ የሚችልበት አሳማኝ ምክንያት የነበረዉ ስለመሆኑ ወይም መቃወሚያዉን ማቅረብ ያልቻለዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ማሳየት ከቻለ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ አገላለጽ ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ወይም ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነገር ግን ከመፈጸሙ በፊት ዉሳኔዉ መብቱን ሊነካ እንደሚችል የሚያዉቅ ወይም ማወቅ የሚችል ሰዉ ዉሳኔ ከተፈጸመ በኋላ በሌላ መዝገብ ላይ የተሰጠን ዉሳኔ በሌላ አዲስ መዝገብ ለማስለወጥ የሚያቀርበዉ ክስ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡

ሲጠቃለል የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት በተሰጠ ዉሳኔ መብቱ የተነካ ሰዉ ዉሳኔዉ ከመፈጸሙ በፊት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ፣ ዉሳኔዉ ከተፈጸመ በኋላ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር ይችላል፡፡ ይሁንና፣ በአንድ በኩል በአንድ ጉዳይ በርካታ መዛግብት በመከፈታቸዉ ምክንያት የዉሳኔዎች ወጥነት እና ተገማችነት ጥያቄ ዉስጥ እንዳይገባ እንዲሁም ክርክሮች ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አኳኋን እንዲጠናቀቁ ማድረግን ዓላማዉ ባደረገዉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አጠቃላይ መርህ፤ በሌላ በኩል በሰዎች ፍትሕ ማግኘት መብት መካከል ያለዉን ዉጥረት ማስማማት የሚቻለዉም ዉሳኔ የተሰጠበትን አንድን ጉዳይ የሚገዳደር ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ ያልተገደበ ሳይሆን ከአቅም በላይ ወይም በቂ እና አሳማኝ በሆነ ምክንያት ዉሳኔዉ ከመፈጸሙ በፊት መብቱን የሚነካ ዉሳኔ መኖሩን ሊያዉቅ የሚችልበት ሁኔታ ያልነበረ መሆኑን ሲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በሰ/መ/ቁጥር 50835 እና በሰ/መ/ ቁጥር 67127 የተሰጡት አስገዳጅ ውሳኔዎች ተሻሽለዋል፡፡
2. አንድ ሰዉ መብቱን የሚነካ ዉሳኔ የተፈጸመ እንደሆነ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችለዉ፣ ከአቅም በላይ ወይም በቂ በሆነ ምክንያት ዉሳኔዉ ከመፈጸሙ በፊት መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ስለመኖሩ ማወቅ ባለመቻሉ ወይም በተመሳሳይ ምክንያት መቃወሚያ ማቅረብ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
3. በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ አምስት ዳኞች ለተሰየሙበት ሰበር ችሎት ተመልሶዋል፡፡